ቆነጃጅት፥ ወይንና ቅኔ...

ከመጻሕፍት አምባ ፪

-በአበራ ለማ

ይድረስ ለሥንኪን ተጠባቢው ዓለማየሁ ታዬ፣ ታለህበት።

ይህች ሂሣዊ ንባብ አከል ማስታወሻዬ ትድረስህ። እንደ ተጋባዥ የሥነ ግጥም የኔታ ሁኜ፣ አንተ ደግሞ የ"ፍካት የሥነ ጽሑፍ ክበብ" ታሊባን* ሁነህ የዛሬ አሥራ ምናምን ዓመታት በፊት እንደምንተዋወቅ ከላክልኝ መልእክት ተረድቻለሁ። የዘሩት በቅሎ፥ አሸቶ፥ ፍሬውም ጎምርቶና በስሎ ከማየት በላይ ላንድ ገበሬ ምን የሚያስደስተው ጸጋ አለ? የኔና ያንተም ትውውቅና ቁርኝት በዚህ ሊመሰል ታድሏልና እሰዬው ነው።

ደገኛው ወዳጃችንና ሞክሼህ ዓለማየሁ ዲባባ ምስጋና ይግባውና (ከምድረ ስዊድን)፣ በሱ በኩል የላክልኝን በረከቶችህን አቀብሎኝ፣ በናፍቆት እንደተገኘ የቡሄ ጥቢኛ እያገላበጥኩ ስኮመክመው ሰንብቻለሁ። **"የዓለማየሁ ሩባያት፥ ሐይኩና ግራፊቲ-Graffiti"** እጄ ገብተዋል።ሥራዎችህን ባነበብኩና አዳዲሶቹን የምርምር ውጤቶችህንና ሙከራዎችህን በተደረሰኩ መጠን፣ ምንኛ ካገሬ የፈጠራና የምርምር አምባ እንዳራቅሁ እየተሰማኝ ውስጥ ውስጤን ብርድ ብርድ ሳይለኝ አልቀረም። ያገሬ ልጆች በተለይም ወጣቶቹ እንዲህ እየረቀቃችሁና እየተጠበባችሁ መሄዳችሁን በማየቴ፣ ተተኪው ትውልድ አንዳች የራሱ የሆነ ጅማሬና ቅጸላም እንዳለው ማረጋገጫ ነውና፣ "ቅኔ ድሮ ቀረ.... ግጥም አከተመ... ምርምርም..." የሚለውን ቀቢጸ ተስፋ ላለመቀጸል መልካም ማስጠንቀቂያ እንደሆነን ልሸሽግህ አልፈልግም። ብርቱና ብርቱ የጥበብን ርቃቂ ዜማ ወግ ባለው መልኩ አሸግነህ የፈርሶቹንና የጃፓኖቹን ልጆች ትሩፋት አቋድሰህናልና ምስጉን ሁን።



ሦስቱ ያለማየሁ አዳዲስ ዓይነት ሥራዎች

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የፋርሳዊውን ድንቅ ባለቅኔ የኦማር ኻያምን **“ሩባያት”** እና የጃፓኖቹን **“ሐይኩ”** ላገርህ ልጆች ማስተዋወቅህ አበጀህ የሚያስብል ነው። አንተም እንደጠቀስከው ሁሉ ጋሽ ተስፋዬ ገሠሠ ቀደም ሲል የኦማር ኻያምን ሥራዎች ተርጉሞ ለገጸ ንባብ አብቅቶልናል። ከጋሼ ተስፋዬም በፊት ሌላ ኢትዮጵያዊ ተርጓሚ የኦማር ኻያምን ሥራ ወዳማርኛ መልሶ እንዳስነበበን ትዝ ይለኛል። ምናልባትም አቶ ቤካ ነሞ የሚባሉ ተርጓሚ ሳይሆኑ አይቀርም ይለኛል ድብቅ ሕሊናዬ። እርግጠኛ አይደለሁም፣ ግን የኦማር ኻያም ሥራ የሆነ፣ ምናልባትም ከሩባያት ግጥሞች ጎራ ወጣ ያለ ለማንበቤ ግን አልጠራጠርም

አንተ በሩባያት ምርምር ፍተሻህ ሂደት ውስጥ አፍታተህ የነገርከንን የጥበቡን ምስጢር፣ ጋሼ ስብሃትም ለጋሼ ተስፋዬ **“መልክአ ዑመር”** በጻፈው መግቢያ ላይ እያዋዛ ከዚህ ዓይነተኛ ቅኔ ጋር ተዋወቁ ሲለን አግኝተነዋል። እንዲህ *አስተዋውቆናል....”አቦይ ኻያም በሚወዷት በትውልድ ከተማቸው በናይሻፑር እና በመላው ፋርስ፥ ሕይወት ያሳያቸውን አውጥተው አውርደው፣ ጥልቀትና ምጥቀት ባለው ግጥም ጻፉት። እሳቸው ብልጭ ሲልባቸው አንድ ወይ ሁለት ባለ አራት መስመር ግጥሞች ነበር የሚጽፉት። ብዙ ጊዜ እዚያው እጻፉበት ቦታ ትተውት ይሄዱ ነበር ይባላል። አንዳንዴ እንግዲህ ወይን ጠጅ ቤት አንድ ሁለት ባለ አራት መስመር ግጥም እየተዉ ይሄዱ ነበር ማለት ነው። አቦይ ኻያም ካለፉ በኋላ፥ በየቦታው ከተዉዋቸው ግጥሞች ሊገኙ የቻሉትን ያገራቸው ሰዎች ሰበሰቡዋቸው። ስብስቡ “ሩብአያት” ተባለ። “ባለ አራት መስመር ግጥሞች” ማለት ነው።...”* ይለናል ጋሽ ስብሃት። (መልክአ ዑመር፥ ገጽ 7)

ይህንን የኦማር ኻያምን ግለኛ ወጥ የቅኔ ፈጠራ ጥበብ አንተም ደሞ ከነ ኤድዋርድ ፊትዝዠራልድና ከመሳሰሉት ያገኘኸውን ተስተምሮ ተንተርሰህ፣ የበኩልህን ማስተዋወቅ ለተደራሲያኖችህ እነሆኝ... ብለሃል። እንዲህም ትነበባለህ ዓለማየሁ... *“ሩባይ ባለ አራት መስመር ግጥም ነው ቢባልም፣ በአገራችን ሲቀኙባቸው እንደኖሩት ባለአራት መስመር መዲናና ዘለሰኛ ግጥሞች አራቱም ስንኞች ቤት እየመቱ ማለትም ሀሀሀሀ (AAAA) ውይም ሁለት ሁለቱ ስንኞች ቤት እየመቱ ማለትም ሀሀለለ (AABB) የሚወርዱበትን አካሄድ የሚከተል አይደለም። በሩባይ ያሰዳደር ሥርአት የመጀመሪያዎቹ ሁለት ስንኞች ከአራተኛው ጋር ቤት ሲመቱ፣ ሦስተኛው ስንኝ ቤት ይደፋና አራተኛው ስንኝ ተመልሶ ከሁለተኛው ስንኝ ጋር ቤት የሚመታበትን አካሄድ የሚከተል ነው። ማለትም ሀሀለሀ (AABA) ....”* ይለናል ገጣሚ ዓለማየሁ ታዬ። (የዓለማየሁ ሩባያት፥ ገጽ ረ?)

ያንተ ያለማየሁ የሩባያት ምንነት ትንታኔ ከጋሼ ተስፋዬ ወይም ከጋሼ ስብሃት ለየት የሚያደርገው፣ ዋንኛውን የተደበቀውን የሩባያትን ምንነቱንና ስሪተ ፍጥርጥሩን አስፈንትተህ ማሳየት መቻልህ ነው። ይህ ደሞ እንደመልካም ዲያቆን ወይም ደቀ መዝሙር “ምስጢር አውቋል” እንድንልህ ግድ ይለናል።

ምንም እንኳን ጋሼ ስብሃት በጋሼ ተስፋዬ የዑመር ኻያም ትርጉም ሥራ መግቢያ ላይ የሩባያትን ባለ አራት መስመር ግጥምነት ብያኔ ቢያጸድቅም፤ በጋሼ ተስፋዬ ሥራ ላይ ግን በዘላቂነት መልኩ ይህንን አናስተውልም። አንዳንዴ ባለአራት፥ አንዳንዴ ባለ አምስት፥

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

አንዳንዴ ባለስድስት፥ አንዳንዴ ባለሰባት ወዘተ... ስንኞች ግጥሞች ባንድ አንጓ (Stanza) ላይ እናገኛለን። አንዱ ስንኝ ካንዱ ቤት እየመታ የሚጨርስ እንጂ፣ ቤት የሚደፋ አመጫት ስንኝ ያንጓው ቤተኛ ስንኞች አስዘንቀው አይታዩም። ያንተ ሩባያቶች ግን መሠረታዊውን የኦማር ኻያምን ስልትና ድንጋጌ ተከትለው፣ ሁሌም ባለአራት ስንኝ ወይም ባለአራት መስመር ሁነው እናገኛቸዋለን። ሳልሳዊውም ስንኝ ከሌሎቹ ተለይቶ ቤት ሲደፋ፣ የመጨረሻው አራተኛው ስንኝ ከሁለተኛው ስንኝ ጋር ሲጣጣምና ቤት ሲመታ ይስተዋላል። በዜማውም ይደመጣል። እስቲ ከጋሼ ተስፋዬ የኻሃም ሩባያት ትርጉም ዋቤ እንጥቀስ...

" ፳

ኢራምብሄረ ጥጌ ከነውብ አጠድዋ
ሰባት ጥምዝ ወርቅ የጃምሺድም ጥዋ
ድራሻቸው ጠፍቷል
ዐፈር ድሜ ገብቷል!
ወይኒቱ ጉንድ ግን፥ ፍሬ ዘለላዋ
(ከመ ዕፅ እንተ ትክልት ሀበ ሙሀ ዘማይ)
... ዝንታለም ነው ወዝዋ!

" ፺

የዳዊት ከናፍር ተገጥመው ባይዘፍንም
በገናዊ ልቡ ትር_ትር ባትልም
በማህየዊ ዜማ ዋኔ ትጮሃለች
"ወይን! ወይን! ቀይ ወይን!
የወየበ ጉንጩን አውዛልኝ" ትላለች።" (መልክአ ዑመር፥ ገጽ 18)

ጋሼ ተስፋዬ ይበልጡኑ የእንግሊዛዊውን የኤድዋርድ ፊትዝዠራልድን ስልት ተከትሎ፣ የኻያምን ሩባያቶች እንደተከታታይ ትረካዎች ለመሰደር መታተሩንና ዓለማየሁ ያስቀመጠውን የግጥሙን መዋቅራዊ ሥንኪን (Structural esthetic) ከፋይዳው አለማስገባቱን ልብ ይሏል። ይልቁንም ለኻያም ሩባያት ይዘቶች ይበልጡን እንደማለለ ከዚህ ከትርጉም ሥራው መረዳት ይቻላል። ባንደኛው አንጓ ላይ ሰባት፥ በሁለተኛው ላይ ደግሞ አምስት ዘለላ ስንኞች መካተታቸውንና ቤት የሚመቱም መሆናቸውን ማስተዋል ይቻላል። ኤድዋርድ ፊትዝዠራልድ የኻያምን ሩባያቶች ለዓለም በማስተዋወቁ ረገድ ቀዳሚውን ሚና ቢጫወትም፤ የራሱን የሩባያት አቀራረብ ሥርዓት በመከተሉ፣ መሠረታዊውን የኻያምን ሩባያት ድንጋጌ በማፍረሱ ይታወቃል። የሱን ፈለግ ጋሽ ተስፋዬ ሲቀጽለው፤ ዓለማየሁ ግን የኻያምን አኩራ እንደጠና ብቅ ብሏል።

ወዳንተ ወደ ዓለማየሁ ሩባያት ስንመለስ ደግሞ፣ በመጽሃፍህ መግቢያ ላይ ያስቀመጥከውን ድንጋጌ እንደምን ጠብቀህ አንጓዎቹን እንዳነጎትካቸው ሁለቱን ላብነት እናስተውል።

" ፳

በሰው ትከሻ ተረማምዶ ከሰው ትከሻ ወጣና
ከሰው ትከሻ ተጣብቆ በሰው ትከሻ ሰባና
'ሰው ማለት ውሻ ነው ይበል!'
አጀብ! ሰው ሰውነቱን ረሳና

፺

የነኮማሪት ገዳም ስንቱን ኮበሌ ከተበ!
አዳሜ ለያም ለፀሎት መንፈሱ ለጽድቅ አደበ
ኮረዶቻችን መነኑ እጸፋርሲቱን ቀመሱ

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ዘርማንዘራቸውም ኮራ በተመክኾ ተደበበ” (የዓለማየሁ ሩባያት፥ ገጽ 6/7)

እኒህ ለናሙና የተጠቀሱ ሁለቱም ያንተ ሩባያቶች፣ በያንዳንዱ አንጓ አራት አራት ስንኞችን ሸክፈዋል። በድንጋጌውም መሠረት ሳልሳዊው ስንኝ ከቀሩት ሶስቱ ስንኞች ተለይቶ አሉታዊ ቤተኝነቱን በቤት ድፋት ይገልጻል።

የሩባያት ግጥሞችን የጭብጥ ምርጫ ስንመረምር ደግሞ፣ እያንዳንዱ ገጣሚ የየራሱ የይዘት ምርጫ እንዳለው እናስተውላለን። ዑመር ኻያም በወይዛዝርትና በወይን ጠጅ እጅግ ፍቅር ዙሪያ የማለለ የባለቅኔ አስተውሎቱን በጅጉ ሲቸረን፣ እንዳንተ ያለው የሩባያት ወጣኒ ደግሞ ሁሉን አቀፍ ጭብጥን ለይዘቱ ዋቤ አድርጓል። ጋሼ አቤም በዘመኑ ትንሽ ከሩባያት ድንጋጌ ፈንገጥ ባሉ ሩባያት መሰል ሥራዎቹ በተለያዩ ጭብጦች ዙሪያ መግጠሙ ይጠቀሳል። አንተ የጠቀስከውም እውቁ አርመናዊ ባለቅኔ ሆቫኔስ ቱምንያንም በጻፈቻ ሩባያት ላይ፣ የሩባያትን ቅርጽ ድንጋጌ ጠብቆ፣ በተለያዩ ጭብጦች ዙርያ መጻፉን ከምሳሌዎቹ መረዳት ይቻላል።



ነገርን ነገር ያነሳዋልና፤ ዑመር ኻያም ባለቅኔ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሌሎች ክህሎትና ተሰጥኦ የነበረው ሰው እንደነበር መላ ምታቸውን የሚሰነዝሩ ተመራማሪዎች ብዙ ናቸው። ከባለቅኔነት ባሻገር የእስላም ባህታዊ ወይም ሱፊ ነበር የሚሉት ሲኖሩ፣ የለም የተዋጣለት ፈላስፋም ጭምር ነበር ብለው የሚያክሉለትም አሉ። ጋሼ ስብሃት ለጋሼ ተስፋዬ በጻፈለት መግቢያ ላይ፣ ይህንን የኻያምን ፈላስፋነት የሚያንጸባርቅ አንድ አፈ-ታሪክ አስነብቦናል። ታሪኩ እንዲህ ነው...

የሰባ አራት ዓመት አዛውንቱ ዑመር ኻያም አንድ ቀን ባንድ ዩኒቨርስቲ ደጃፍ ሲያልፉ፣ (እዚህ ላይ ላዛውንትነት ሰብእና ዋጋ ለመስጠት አንቱታን መርጫለሁ) ውስጡ ለሚካሄድ ጥገና ድንጋይ የተሸከመ አህያ በጌታው እየተነዳ መጥቶ፣ ካጥሩ ገረገራ ደጃፍ (ከተምበሪ)ድንገት ገተራል። ጌታው ወደ ዩኒቨርስቲው ግቢ ግባ ብሎ ቢገርፈውም ቢያስገድደውም አሻፈረኝ ይላል። ይሄኔ አዛውንቱ ዑመር ኻያም ወዳህያው ጆሮ ጎምበስ አሉና የሆነ ነገር አንሾካሾኩለት። ይሄኔ ያ እምቢ ባይ አህያ ሰተት ብሎ ወደ ዩኒቨርስቲው ግቢ ይገባል።
በዚያ ያልፉና ሁኔታውን ያስተውሉ የነበሩ ሰዎች፣ “ጌታው ምን ቢሉት ነው የገባው?” ብለው ይጠይቋቸዋል ኻያምን።

“ባለፈው የህይወት ዘመኑ ይህ አህያ ሰው ነበረ... “ ብለው መለሱ ጌታው።

“እንዴት?” ብለው አጥብቀው ጠየቁ ሰዎቹ።

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

“ይሄ የዛሬው አህያ የትናንቱ ሰው፣ እዚህ ዩኒቨርስቲ እጅግ የተከበረ ፕሮፌሰር ነበር። በገዛ ቤቱ በገዛ መንበሬ እንዴት አያውቁኝም? ብሎ በመናደዱ ነበር አልገባም ማለቱ… ዋ!… የሰው ያህያ ነገር…” ሲሉ መለሱ ኻያም።

“እና እርስዎ ምን አሉትና ገባ?” ምክንያቱን ለመስማት ጆሯቸው ቀመ ሰዎቹ።

“ባንዲት ሩባያት ግጥሜ ነገርኩት። ‘አይዋ ጺምዎ ወደ ጭራ ቢለወጥም ብዬ ጀመርኩና… ፕሮፌሰር… ፕሮፌሰር… እባክዎትን ወደ ቤትዎ በክብር ይግቡ…’ አልኩት በጆሮው። እናም ሰተት ብሎ ገባ…” አሉና መለሱ ኻያም።

ከዚህ በኋላ አንገታቸው ወደ መዲናዪቱ ሳይቀና፣ ጭው ወዳለ በረሃ ተጉዘው እንደወጡ መቅረታቸውን ጋሽ ስብሃት ተርኮልናል።

ያፈታሪኩ ምጸታዊ አንድምታ ለዘመናችን አንዳንድ አድርባይና ካብ አይገቤ ምሁራን መልካም ጠቅታ ነውና፤ ባለቅኔውንና ፈላስፋውን ዑመር ኻያምን ከሰባት መቶ ዓመታት በኋላም እንደተደረስናቸው ልብ ይሏል።

ወዳንተው ወዳለማየሁ ሩባያቶች ሥነ ውበታዊ እሴቶች (Aesthetic value) ላተኩር…

ያንተን ሩብያት ባንድ ትንፋሽ አንብቦ ውስጠ ምስጢሩን መደረስ እንዲህ ቁልቁለት ሆኖ አላገኘሁትም። እንዳለቃ እምባቆም ቅኔ አዘራረፍና አቀራረብ መለስ ቀለስ እያሉ ማዋዋት የግድ ይላል። እንዲያ ከሆነ ማለፊያ የቅኔዎችህ ተደራስያን ለመሆን የተመቻቸን እንሆናለንና ነው። ያጫርካቸው አዳዲስ ጭብጦችና ዘይቤዎች ይበልጥ እንድንመረምርህ፥ እንድናውቅህ፥ እንድንጠጋህ የሚያተጉን ናቸው።

አሁን እስቲ እነዚህን ለምርቃት ያህል ልጠቃቅስና ወደ ሐይኩና ግራፊቲ ሥራዎችህ ልሸጋገር ደሞ….

“ ፵፫

በተቀናው ምንገዴ ላይ ጉርብጥብጥ ገደል የቆፈርከው

በተደላደለው ምኝታዬ የሾህ ድብዳብ ያነጠፍከው

ደክመህ ባዝነህ ወንድምዬ ግቤን አሰመርክ እንጂ

ፀአዳ ድንግል ህሊነዬን የቂም ጥላሸት አልቀባኸው” (የዓለማየሁ ሩባያት፥ ገጽ 45)

አየኸው **“የሾህ ድብዳብ”** የሚለው ተለዋጭ ዘይቤ (Metaphor) ምን ያህል ገዝፎ ባንጓው ውስጥ እንደሚደመጥ? ወዳጅ ያሉት ሰው ደክሞ ባዝኖ፥ ይህን የመሰለ ድብዳብ አንጥፎ ላስተኛህ ካለህ፣ እንግዲያ ተዬ ወዲያ እንዴት ብለህ ግብሩን ትገልጥ?! ግሩም ነው።
ደሞ ይህን አየሁልህ…

“ ፵፪

አንዳንዱን ሲፌጥሬው ኬ ቂንጪላት ቤኩል ያጣሚሞውና

ሚላሱን አርዚሞ ቴንኮሎን ቆሊሎ ይኬዊኔውና

ቤሴው ፍቂር ኢጠት ጤግቦ ሪሃብቴኛ ሌብሶ ዬታሬዜ ሆኖ ይኖራታል

ከሺሙጥ ኬኪፋት ኬኢኩይ chemicals ቴቄሚሟሊና” (የዓለማየሁ ሩባያት፥ ገጽ 46)

አጀብ ነው!… ጭብጥነሽ፥ ቅርጽነሽ፥ ቋንቋነሽ፥ ዘዬ ነሽ… ምን ያልተካተተ የሥንኪን እንቁጣጣሽ ዓይነት አለ እዚህ አንጓ ውስጥ?!!! ምንም። አንዳንዴ በመረመሩህ ቁጥር እሩቅና እሩቅ እየሆንክ አባይን በጭልፋ ታስብላለህ። መምህር ሣሙዔል አዳል እንዳየህ ሁሉ እኛም

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

እያየንህ ነን። ስመ ጥሩው የሥንኪን ተመራማሪና ሃያሲ ጋሼ አምሃ አስፋው ተወደ ሰሜን አሜሪካ እንደምን አይቶህ ይሆን? እንዲህ በትንሹ የሚጠግብህ አይመስለኝም። ያሜሪካ ድምጹ አፍቃሬ ጥበብ ጋዜጠኛ አሉላ ከበደ፣በቅርቡ ካንተ ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ ላይ፣ ይህን አዲስ ጅምርህንና ትኩረትህን ትበረታበት ዘንድ ማትጋቱ ያለዋዛም አልነበረም። ካይን ያውጣህ ጭምር ሊልህ እንጂ...

በነገራችን ላይ አዲስ አበባ መሃል ፒያሳ፥ ከመብራት ኃይል ዋና መሥሪያ ቤት ጥቂት ወረድ ብሎ የሚገኘውን የዑመር ኻያምን ክላሲካል ሬስቶራንት በፍቅር እናዘወትረው የነበርን ቤተ ጸሐፍት ጥቂት አልነበርንም። ጋሼ ብርሃኑ ዘሪሁንና ጋሼ መንግሥቱ ለማ ሁነኛ የወዳጅ ቀጠሮ ሲኖራቸው እዚያ ይመቻቸው እንደነበር ምስክር ነኝ። በግሌ ከነበረኝ ደምበኝነት ባሻገር፣ ተሁለቱም ጋር የቆይታ እድል አግኝቼበት ስለነበር ትዝታዬ ብርቱ ነው። ጋሽ ተስፋዬን፥ ጋሽ ስብሃትን፥ ያኔ ያኔ እዚያ ያፈላለጋቸው አያጣቸውም ነበር...

ካንድ አሠርት ዓመታት የውጭ ቆይታ በኋላም አዲስ አበባን በወፍ በረር ስመደንባት፣ የዑመር ኻያምን ሬስትሮራንት ሀጇ በናፍቆት ተሳልሜዋለሁ። በካሜራዬ ያስቀረሁት ምስልም ይህንኑ ያውጃል። ግን ግን ያንን ነባር ሬስቶራንት ማን ለምን "ዑመር ኻያም" ብሎ ሰይሞ እንደከፈተው ምስጢሩን ሳላውቅ መቆየቴ ሁሌም ይቆጨኛል። ምናልባትም አንድ ፋርሳዊ ወይም አንድ ታላቁን ባለቅኔ ዑመር ኻያምን የሚያደንቅ ያገራችን ሰው ወይም አንድ አፍቃሬ ወይዛዝርትና ወይን ጠጅ የድሮ አራዳ ... ከፍቶት ይሆን? እኔጃ!.. ያዲሳቦቹ ጠሓፍት ይህን ጉዳይ አጣተው አንድ ደህና መጣጥፍ ያቀብሉን ይሆናል። የሚገርመው ደሞ በብዙ አገሮችም በዑመር ኻያም የተሰየሙ ምግብ ቤቶችና የወይን መጎንጫ ቤቶች እጅግ ብዙ መሆናቸው ነው።ታዲያ የሁሉም ልዩ መለዮ ከምግብ ጋር ወይንን መሸማቸው ነው። http://www.omar-khayyam.co.uk/indian-restaurant/indian-restaurant-edinburgh-omar-khayyam.jpg

የሸገሩ "ኦማር ካያም ምግብ ቤት"

ዓለማየሁ... ወደ ሐይኩ ሥራህ ልራመድ። ይህ ደሞ ከጃፓኖቹ ባለቅኔዎች "ዋሸራ አምባ" ወዲህ ብለህ አዲስ እያስተዋወቅኸን ያለ ሌላው ብርቱ ሥራህ ነው። ሐይኩዎችህንም ባማርኛና በ'ንግሊዝኛ ቋንቋዎች ተጠብበህ እንዳቀረብክልን ይስተዋላል። መልካም እርምጃህንም ከሥራህ እያየን ለትጉ ደቀ መዝሙርነትህ ይሁንታችንን ቸረናል። ታንተው እመጽሃፍህ መግቢያ ላይ እንደተደረሰኩት ከሆነ፣ ሐይኩ የመነጨው ከጥንታዊው የቡዳ መነኮሳት በጋርዮሽ ከሚዘርፉት "ሬንጋ" የተሰኘ ቅኔ ማህጸን ነው።

የዚህ ቅኔ ዓይነተኛ መክፈቻ የሆነውን "ሖኩ" የተባለውን ባለ ሦስት ቤት ስንኝ፤ ማትሱኦ ባሾ የተባለው አፈንጋጭ ጃፓናዊ ባለቅኔ፣ "ሐይኩ" በሚል መጠሪያ ጡት አጥብቶ እንዳሳደገውም

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

አመልክተህናል። ከዚህ የምንማረው እንግዴ የሐይኩ ዓይነተኛ ጠባይ ባለ ሦስት ቤት ቅኔ ብቻ መሆኑን ነው። አክለህም ሐይኩ ፋይዳዬ፥ ጉዳዬ፥ ጭንቀቴና ጥበቴ ብሎ የሚያበክረው ጭብጥ ተፈጥሮና የተፈጥሮ ጉዳይ ብቻ እንደሆነ ጃፓኖቹ ማትከናቸውን አደራ ብለኸናል፥ እንቀበላለን። አዲስ ዓይነት እይታ በመሆኑም፣ ባማርኛ የቅኔ ዘረፋ ዓለም ውስጥ ተፈጥሮን ብቻ እየነቀስን እንድንጠበብበት የነማሳኦካ ሺኪ ደቀ መዝሙር ሆነህ ሙከራዎችህን አካፍለኸናል። የሐይኩንም አቀኛኘት ድንጋጌ እንድንጠብቅ ሕጉን እንዲህ ስትል አመላክተህናል።

“የሐይኩ Traditional ቅርጻዊ አሠዳደር ዓይነተኛ ምሳሌ ተብሎ የሚገመተው፣ በሦስት መስመሮች የተወሰነና በመጀመሪያው መስመር አምስት፥ በሁለተኛው ሰባት፥ በመጨረሻው እንደገና አምስት የጃፓንኛ KANA ወይም የእንግሊዝኛ SYLLABLEን በድምሩም 17 KANA/SYLLABLEን ያካተተ ቅኔ ነው።” ያልከን፥ የሐይኩን ውስጠ ማንነት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው። (ሐይኩ _ HAIKU፥ ገጽ 4/5)

የሰጠኸንን የእንግሊዝኛ ሐይኩ ቅኔ ላብነት እዚህ ታደባባዩ ብናሰጣው፣ የቅርብ እማኝ አገኘን ማለት ነው። እንሆ…

“portrayed in a pond (5 syllables/ቀለማት)
nature exhibits her nude (7 syllables/ቀለማት)
clean obscenity” (5 syllables/ቀለማት) (ሐይኩ _ HAIKU፥ ገጽ 5)

ታዲያ ታንተ የምርምር ውጤት ልንረዳው የቻልነው ለጃፓናዊው ሐይኩ ሕላዌ 17 ቀለማት/KANA/SYLLABLE የግድ የሚለውን (5+7+5) እንግሊዝኛው ከ11 ቀለማት/KANA/SYLLABLE በላይ አለምፍቀዱን ነው። ባማርኛም ቋንቋ ባህሪይ ምክንያት ሕይኩን በ11 ቀለማት/KANA/SYLLABLE መሥራት አለመቻሉን ተረድተናል። ስለዚህም አንተ ከደረስክበት የፍተሻ ድምዳሜ በመነሳት፣ አንዳንድ ቋንቋዎች ልክ እንደጃፓኑ ሐይኩ ዓይነት ባለ17 ቀለማት/KANA/SYLLABLE ሐይኩ ሊቀኙ አለመቻላቸውን እንረዳለን። ያም ሆኖ ባለ ሦስት ቤት ስንኙ ውበት ለሐይኩ ሐይኩነት እንደተጠበቀለት እንዲቆይ የጋራ ስምምነት እንዳለ ከራስህ ሥራ ማስተዋል ተችሏል። ይህም ሲባል ዋናው የሐይኩ አይዝረከረኬነት፥ ቁጥብነት፥ ቀለል ያሉ ቃላትን መምረጡና የምስል ጓዳነቱ ዐቢይ መለዮው መሆኑንም ሳናሰምርበት አናልፍም። እስቲ ከሐይኩው መጽሃፍህ እኒህን ባሕሪያቱን አጉልተው የሚያሳዩትን ሐይኩ ግጥሞችህን ካማርኛውም ከ’ንግሊዝኛውም ጥቂት ላብነት ያህል ልጥቀስ።

2
የደመና መዘምራን
እያሸበሸቡ በእልልታ ሲዘምሩ
የደመና መዘምራን

39
ሲመሻሽ
ርግቦች በሕብረት እየበረሩ
ጀምበሪቱን ሸኙ

63
አበቦች
እንደረገፉም አደብ ገዝተዋል ንፋስ
ስደት ሄዷል

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

27
winter
bare branches scranching the sky
spring, is but a dream

30
the snail
all out of its shell waves to me
his jelly horns

ከሐይኩ የቅኔ ስብስብህ በፊት በ□ሺ.ህ ዓ.ም. ለገጸ ንባብ ያበቃኸው "**ግራፊቲ** - Graffiti" የተሰኘው ባለክልዔ ልሳን የግጥም መድብልህ ሌላው ተጠቃሽ ሥራህ ነው። በዚህ መድብል ወስጥ የምናያቸው አዲስ በቀል አሰነኛኘትና ጭብጦች አዲስ ያማርኛ የግጥም አገጣጠም ጥበብን አዲስ አሻራ የምናስተውልበት ነው።

ጋሼ ሰሎሞን ደሬሳ በሺ.፱፻፷፪ ዓ.ም. "ልጅነት" በተሰኘው የግጥም መድብል ሥራው አዲስ ያገጣጠም ስልትንና አተያይን እንዳስተዋወቀን ሁሉ፣ አንተም የራስክን አዲስ ዓይነት አቀራረብ በዚህ ሥራህ ላይ አሳይተህናል። ጋሼ ሰሎሞን "ዘበት እልፊቱ፥ ወለሎታ"ን ከብዙ ብዙ ዝምታና የስደት ሕይወት በኋላ በሺ.፱፻፺፩ ዓ.ም. በዚያው በራሱ ስልት እንደደገመንም ልብ ይሏል። የያኔው የጋሼ ሰሎሞን ሥራም ሆነ የዛሬው ያንተ ግራፊቲ፣ ከነባሩ ያማርኛም ሆነ አገርኛ ያገጣጠም ስልት ወጣ ብለን ሌላ ሌውንም ሁሉ በየራስ ብጤት እንሞክር የሚሉ ናቸው። የፈጠራን ሥራ በፈጠራነቱ እስከተቀበልን ድረስ፣ ባሮጌው ብቻ ከማዝገም አዳዲሱን ዓይነትም መሞከርና የራስን ተደራሲ መፍጠሩ ክፋት የለውም። ጋሼ ሰሎሞን ያኔ ባዲስ ያገጣጠም ስልቱ ብቅ ሲል እንደጋሼ አቤ ጉበኛ የመሳሰሉትን ጎምቱዎች ቢያስቆጣም፣ የዩኒቨርስቲዎቹን እነዮሃንስ አድማሱን፥ ኃይሉ ገሞራውን፥ ዮናስ አድማሱን፥ ደበበ ሠይፉን... ሳያማልል አልቀረም። እናም ዛሬ ከሦስት ዐሠርት በላይ ተቆጥሮ ሲታይ ጋሼ ሰሎሞን የራሱን አንባቢያን ማፍራት መቻሉን እንረዳለን። እናም አንተም የራስህን ተደራሲያን የማታፈራበት ምክንያት የለምና አበጀህ እንጂ ሌላ ሊልህ የሚችል እንደሌለ እርግጠኞች ነን።

እስቲ ግራፊቲህን ላዳዲስ ተዋዋቂ አንባቢዎችህ ያንተኑ ብእር-አንደበት ላንዴ ልዋስና ላስተዋውቅ። ዓለማየሁ ግራፊቲን እንዲህ ያቀርብልናል...

"ግራፊቲማ በየአጥሩ በየግድግዳው በየመጸዳጃ ቤቱ በየጠረጴዛና ወንበሩ... ወዘተ የሚጣፍ ወይም የሚሳል ጠሐፊው ወይም ሰዓሊው (አብዛኛውን ጊዜ) ያልታወቀ (ሕገ ወጥ) ጽሁፍ ወይም ሥዕል ነው። ከላይ በተጠቀሰው ግርድፍ ብያኔ መሠረት ግራፊቲን "ክታበ ሙስና" ወይም "ሥዕለ ሙስና" ብሎ መተርጎም ይቻል ነበር። ግና ግራፊቲ በራሷ ለሐበሻ ምላስ የማታዳልጥ ለጆሮውም የማትጎረብጥ ሸሙንሙን ያለች ባለ አራት ፊደል ቃል ናት።" (ግራፊቲ፥ ገጽ 5?) ብለኸናል ዓለማየሁ። እኛም ድንጋጌህን ተቀብለናል። በራስህም መስፈርት ልናይህ የግድ ግድ ይለናል።

እናም ግራፊቲ እንድ አዲስ ዓይነት ከተለመደው ያማርኛ ግጥም አገጣጠም ድንጋጌ ያፈነገጠ ሥራ ነው ማለት ነው። በወል፥ በስንጎ መገን፥ በመዲና፥ በጸጋዬ ቤትኛ ወዘተ... ዓይነት የማንፈርጀውና የማንመረምረው የግጥም ሥራ ነው ማለት ነው። እንግዲህ ዓለማየሁ ከተለመደው ቤት አፈነገጥክ ማለት ነው... ያራስህን አንባቢ የራስህን ደቀ መዛሙርት እንደጋሼ ሰሎሞንና እንዳንዳንዶች ሁሉ ፈጥረህ ትጓዛለህ ማለት ነው። ጥቂት ከግራፊቲ ሥራዎችህ እንቀማምስልህና መንገዱን .... ምን ያርግልህ ብለን እንመርቅሃ?!...

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

“ተጠየቅ

ሃሳብ ሸክም ሲሆንብህ
ታካፍለዋለህ
ሕይወት ሸክም ብትሆንብህ
ራስህን ታገላለህ
ትእቢት ሸክም ቢሆንብህ
ፈጣሪን ታማለህ
ምላስ ሸክም ቢሆንብህ
ወዴት ትደርሳለህ?

ጥቅምት 1992”

* * *

ዘመናዊ ኩምክና

የቀማኛ ለቀማኛ መቀማማት
ያሚተኛ ላሚተኛ መተማማት

ኅዳር 1996

* * *

ለዓለም ፪

ዳውንታውንሂ ጉድ አፀድ
የትፍስህት የርካታ መንደር
የኃጢያት ወ የስርየት
የሕላዌ ፍኖት ከተምበር
ዘንድሮ ነገር አመጣ
ጣእሙ ኮነ ጉራማይሌ
አሕዛብም ጉድ ተሠራ
ስኳር ሲሻ ልሶ አሞሌ

መጋቢት 1991
ለአቤ ጉበኛ

* * *

የክር
ስቶስ
ትእዝብት በመስቀሉ
ላ
ይ
መ
ቃ
ብ
ር

ጥር 1996

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

*   *   *

ማጉረምረም

የድምጾች ቅንብር ፍሠት
አንድምታ አልባ ግርግር
የድምጾች ቅንብር ፍሠት
አንድምታ ሙሉ ክርክር
ማጉረምረም

ታህሣሥ 1993"

እንዲህ እንዲህ እያልን ያንተን ያለማየሁን የግራፊቲ ትሩፋት እየመዘዝን እንደየራሳችን ብጤትና ግንዛቤ መደረስ እንችላለን፡፡ ግጥም ለተደራሲ የሚለግሰው ትልቁ ጸጋ "በራስህ መንገድ እንደፈለከኝ ተርጉመኝ፥ ፍታኝ፥ ፈልቅቀኝ.፥ ተደረሰኝ..." ማለቱ ነው። አንድን የግጥም ሥራ ይዘቱ ይሄና ይሄ ብቻ ነው ብሎ ብያኔ መስጠት፣እንኳን ለተደራሲው ለገጣሚውም ለራሱ የተሰጠው መብት አይደለም። ዘመን በተለወጠ፥ መቼት በተቀየረ፥ ትውልድ አልፎ ትውልድ በተተካ ቁጥር የሚሰጠው አንድምታ ያራሱ ፍቺ፥ ያራሱ ቃና፥ የራሱ ለዛ ያለው ነው እሚሆነው። ያለዚያማ የሥነ ግጥም ፋይዳው፥ የቅኔ ወዝና ወለላው ምን ሊሆን ነው?!... እናም ያንተን ግራፊቲም እንዲህ እንዲህ እያደረግን መቋደስና መፈትሽ የኛ ፈንታ መሆኑ ነው። በዚህ ግራፊቲ ብለህ በሰየምከው መድብልህ ውስጥ እፍኝ ሙሉ በቅርጽም በይዘትም አዲስነት ያላቸው ሥራዎች ይታያሉና፣ ቀጣይ ሥራህን መናፈቃችን አልቀረም።

ይህን ሂሣዊ ንባብ መሰል ጦማሬን ከመቋጨቴ በፊት፤ ስላንዳንድ ዘመንተኞችህ ብርቱነት ጥቂት ማስታወስን ወደድኩ። ከሸገርም ከባሕር ማዶም ብቅ ብቅ ያሉ ያንተ የእድሜ ዘመንተኞች ጥቂት ገጣሚያን አሉ። ጥቂት ያልኩት በጥራት አኳያ ስመዝናቸው ተድርጎ ይመዝገብልኝ፡፡ በአሃዝ ከመጣን በተለይ አገር ቤት የግጥም አዝመራ ሃድራ የገባበት ዘመን እስኪመስል ድረስ፣ ብዙ ገጣሚያን ሥራዎቻቸውን ላይነ ንባብ እያበቁ መሆናቸውን እየተረዳን ነው። ግጥም በባህሪው እጅግ ጠሊቅ፥ ሁለመናው ቁጥብጥብ ያለ፥ ሉዓላዊ ቋንቋን የሚጠቀም አስቸጋሪው የሥነ ጽሁፍ ዓይነት መሆኑ ላዳዲሶቹ ገጣሚያን ዳገት የሆነ አይመስልም። ምናልባትም የዘመናችን ወጣት ጸሐፍት ግጥምን እንደጥንተኞቹ ያገራችን ከብት አጋጆች (እረኞች) የሕዝብን ብሶትና ስሜት የማውጫ ሁነኛ ቀልጣፋ መንገድ አድርገው አግኝተውት ይሆን? ማን ያውቃል፥ ይሆን ይሆናል... ግና የጥራቱን ነገር አደራ የሚሉ ተደራሲያን ተማጽኖም ችላ ሊባል አይገባምና ቆም እያሉ እርስ በርስ መናበቡ አይከፋም።

ላነሳሳቸው ወደ ወደድኳቸው አንዳንድ የዘመን እኩዮችህ ገጣምያን ልለፍ። ይሄ በእውቀቱ ሥዩም የሚባል አዚመኛ ሁሉን አወቅ ገጣሚ፥ ጣፊ፥ ፌዘኛ፥ ቧልተኛ... ኧረ ምኑ ቅጡ! ስንቱን ክህሎቱን አንስቼ ልዘለቀው ወንድም አለም? እንዲሁ በደፈናው ለዘመናችን የተበረከተ አዲስ ፈር ቀዳጅ ሌላው የጥበብ ማእድ በረከታችን ነውና ይበርታበት በጅምሩ። ያ ወጣት ገጣሚና አጫጭር ልቦለዶችን አሸጋኝ ጣፊ እንዳለ ጌታ ከበደ፥ የጥንት የጠዋቷ ፀሐይ መላኩ፥ ያዋሳው የ60 ሻማዎቹ ሙሴ ዘላለም ጌታቸው፥ የስሜን አሜሪካው ቴዎድሮስ አበበና ያልታተመው የስዊድኑ ዓለማየሁ ዲባባ ላይነት ያህል ከሚጠቀሱት መካከል ናቸው። ያስ ወንድዬ ዓሊ እጁ ተምን ይሆን? ሌሎችም ምናልባትም ሥራቸውን ለማየት ያልታደልኳቸው ጎበዝና ጎበዛዝት ይኖሩ ይሆናልና ሊበረታቱ ይገባቸዋል። እኒህ ከላይ ስሞቻቸውን ላይነት ያህል ያነሳሳኋቸው ግን፣ ያማርኛን ዘመናዊ ሥነ ጽሁፍ እድገት በተለይም ከሥነ ግጥምና ካጫጭር ልቦለዶች አኳያ እየታደጉ ያሉ ብርቱ ያገር ልጆች መሆናቸውን ሳላሰምርበት አላልፍም። መልካም ጅምራቸውን እዳር ያደርሱ ዘንድና እንዲህ እንዳንተው አዳዲስ ሙከራቸውን ሁሉ "እጃችን ከምን..." ይሉን ዘንድ ተስፋዬ ነው።

**ታሊባን ... ተማሪ ወይ ደቀ መዝሙር እንዲሉ ባረብኛው።*

ablemma@gmail.com

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com